# ኢንስቲትዩትቱ የስልጠና ማስፋፊያ 18ሺህ ካሬ ቦታ ተሰጠው





አንጋፋው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዘርፉን የሚመጥን እንዲሁም ከጊዜው ጋር የሚራመድ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ 18ሺህ ካሬ ቦታ ተረክቧል፡፡

ቦታውን የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና የክ/ከተማው የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች በተገኙበት ጉብኝት ተደርጓል፡፡

አሁን ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረትን ተከትሎ ኢንስቲትዩቱ በሀገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ሙያዎች ስልጠና፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር አገልግሎት በመስጠት የልህቀት ማዕከል ለመሆን እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ የሚደግፍ መሆኑ ተገልጿል፡፡

# ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከታንዛንያ አቻው ጋር ተፈራረመ





ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከታንዛንያ አቻው ናሽናል ቱሪዝም ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ።
ከቱሪዝም ማሰልጠኛ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ክቡር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እና ከናሽናል ቱሪዝም ኢንስቲትዩት ዶ/ር ፍሎሪያን ሜቲ ፈርመውታል።

## የታንዛንያው ናሽናል ቱሪዝም ኮሌጅ  ዋና ዳይሬክተር ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን ጎበኙ



የታንዛንያው ናሽናል ቱሪዝም ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ፍሎሪያን ሜቲ እና የሥራ ባልደረባቸው ሚስ ትረስ ሙቹሪዛ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን ጎበኙ፡፡

ዶ/ር ፍሎሪያን ሜቲ ኢንስቲትዩቱን በጎበኙበት ወቅት እንደተናገሩት ተመሳሳይ የአመሰራረት ታሪክ ያላቸው እና በተመሳሳይ በቴክኒክና ሙያ የሥልጠና መስክ የሚሰሩ መሆኑ በጋራ በርካታ ሥራ መሥራት የሚችሉ መሆናቸውን እና በአጭር ጊዜ ወደተግባር እንዲቀየር እንደሚሰሩም ሁለቱም ኃላፊዎች ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡

ይቀጥላል ⇨








አፍሪካ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ የቱሪዝም ሃብቶች ባለቤት ስትሆን ከነዚህ ሀገራት ውስጥ አሁን በጋራ ለመሥራት ስምምነት ላይ የደረሱት  የታንዛንያው ቱሪዝም ኮሌጅ እንደ ኢትዮጵያው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ሰልጠና በመስጠት ግማሽ ምዕተ ዓመትን ተሻግረዋል፡፡ በታሪክም የአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በቀኝ ግዛት በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ለነጻነት ትግሉ ያበረከተችው አስተዋጻኦ እና ስለ ፓን አፍሪካኒዝም ምስረታ ሲጠቀስ ከቀዳማዊ ንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ ጋር ስማቸው ከሚጠቀሱ ጥቂት የአፍሪካ መሪዎች የታንዛያው ጁሊየስ ኔሬሬ አንዱ ናቸው፡፡

እነዚህ ከ55 ዓመት በላይ የስልጠና ልምድ ያላቸው መንግስታዊ ተቋማት የሚሰጡት የስልጠና ዘርፍም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው፡፡ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሪክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እና የኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር ፍሎሪያን ሜቲ (ዶ/ር) በዘርፉ በጋራ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የማማከር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ልምዶችን መለዋወጥ፣ የአሰልጣኝ እና የሰልጣኝ የልምድ ልውውጥ፣ የሥርዓተ ትምህርትና ስፖዚየሞችን በጋራ ማካሄድ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ የመግባቢያ ስምምነት ከተፈራረሙባቸው  ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ የሁለቱም ተቋማት የመግባቢያ ስምምነት በወጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ክቡር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ(ዶ/ር) እና የታንዛንያው የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አምባሳደር ሞህመድ ጣቢት ፈመርተውታል፡፡

# ኢንስቲትዩቱ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ባህል ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ጋር በመተባበር የዓለም ቱሪዝም ቀንን በቦንጋ ከተማ በተለያዩ ዝግጅቶች አከበረ

*ህዳር 5/2017 ዓ ም*






የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ ክልላችን ጭስ አልባው ኢንዱስትሪ ሳይነካ የሚገኝበት፤ ሰውና ተፈጥሮ ተግባብቶ ለአዕምሮ ሰላምን የሚሰጥ አረንጓዴ አሻራ የሚገኝበት መሆኑን በመጠቆም ይህንን እምቅ ሀብት እንደሚፈለገው አልተጠቀምንም ሆኖም አሁን የተጀመሩ ሥራዎችን በማስቀጠል ከፌዴራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል ብለዋል። ይህንን ፕሮግራም ላዘጋጁ ተቋማትና ግለሰቦች ምስጋና አቅርበዋል።
የፌደራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ፕሮግራሙን አስመልክቶ የዘንድሮ የዓለም



ቱሪዝም በዓለም 45ኛ በሀገራችን 35ኛ ጊዜ በሚከበረው '**ቱሪዝም ለሰላም**' በሚል መሪ ቃል ነው። ይህንን ዝግጅት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንድናከብር ክልሉ የቡና፣ የልዩ መልክዓ ምድር እና የተፈጥሮ መስህብ፣ የማርና ቅመማ ቅመም ሀብት ያለው አካባቢ በመሆኑ ቱሪዝሙን በማነቃቃት ለአካባቢውም ሆነ እንደ ሀገር ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እና ለዓለም ለማስተዋወቅ ጭምር እንደሆነ ተገልጿል።



ቱሪዝም ለሥራ ዕድል ያለው ፋይዳ በሚል ርዕስ የተጠና ጥናታዊ ጹሁፍ በተቋሙ ከፍተኛ ባለሙያ በአቶ አህደር ጠና አቀርቧል። ቱሪስቶች ቢመጡ ወደ ክልሉ ምን ያህል ጊዜ እንደሚያሳልፉና የጉዞ ፓኬጅ ሰነድ የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አብይ ንጉሴ አቅርበዋል።
በዚህ ፕሮግራም በክልል የሚገኙ ስድስት ዞኖችና ባህላዊ ምግቦችን በተመለከተ የተሰራ ሰነድ ያቀረበው የተቋሙ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ መለሰ ወርቁ ሲሆን ከተጠኑት ምግቦች ወደ ኢንተርናሽናል ሆቴሎች ለማስገባት የተጀመሩ እናዳሉ እና የቀሩትንም የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ገልጿል፡፡
ሌላው ከቦንጋ ዩንቨርስቲ አቶ ሰለሞን በተመሳሳይ ቱሪዝምን ወደ ሥራ እድል እንዴት መቀየር እንደሚቻል የሚገልጽ ሰነድ አቅርቧል። በቀረቡ ሰነዶች ውይይት ተደርጎበታል።

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ያለውን የቱሪዝም አቅም ማሳየት የሚችል ጥናት፣ የጉዞ ካርታ እና የጉዞ ጥቅል መዘጋጀቱ ተገለጸ፡፡



ህዳር 04/2017 ዓ.ም
የፌዴራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኝ እምቅ የቱሪዝም ሀብትን ለማስተዋወቅ የሚያስችል ጥናቶችን ከክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ጋር በመተባበር እየሰራ ይገኛል፡፡

በአካባቢው ላይ የሚገኙ እምቅ አቅሞች የሚያሳይ ጥናት፣ ይህን በመከተል የጉዞ ካርታና ቱር ፓኬጅ መዘጋጀቱን የጠቀሱት ጥናቱ ከተሳተፉት መካከል የኢንስቲትዩቱ ምርምር ባለሙያ አቶ አህደር ጠና ክልሉ ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት ያለው ቢሆንም እንደ ሀገር በቂ ጥናት ተሰርቶ በሚገባው ልክ ለዓለም አላሳየንም ይላሉ፡፡



አካባቢው የተፈጥሮ፣ ታሪካዊና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም ሀብቶችን የተጎናጸፈ ነው ብለዋል። በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ አሁን የተጀመሩ ሥራዎች እንደ ሀገርም ሆነ ለክልሉ የቱሪስት ፍሰትን ይጨምራል፣ ማህበረሰቡም ከቱሪዝም ተጠቃሚ የሚሆንበት እድል ይፈጥራል።

ከተጠቀሱት ጥናት ሥራዎች በተጨማሪ የምግብ ቱሪዝምን ሊያጠናክር የሚችል በክልሉ የሚገኙ ዞኖች ባህላዊ ምግቦች ሰነድ ዝግጅት መደረጉንም አቶ አህደር ገልጸዋል፡፡ በተለይ ይህ የምግብ ዝግጅት ሰነዶች መዘጋጀታቸው፣ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን በጠበቁ ሆቴሎቻችን ውስጥ ኢትዮጵያዊጣእም ያላቸውን ምግቦች ቱሪስቱ እንዲያገኝ እድል ይፈጥራል የሚሉት አቶ አህደር ጠና የሀገራችንን ምግብ ቱሪዝም ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡



ከተሰሩት ሰነዶች መካከል የስድስት ዞኖች ቱሪስት ማፕ፣ የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ እና አጠቃላይ የክልሉ ቱሪስት ማፕ መሰራቱን የገለጹት ባለሙያው የክልሉን ገጽታ የሚቀይር ትልቅ መሰረት የሚጥል ስራ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከክልሉ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ጋር በመተባበር እያከናወናቸው የነበሩ ስራዎችና የአካከባቢውን ቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማሳደግ የሚያስችሉ ጉዳዮች በህዳር 05/2017 ዓ.ም በቦንጋ ከተማ የምክክር መድረክ ተካሂዷል፡፡

## የኢንቲትዩቱ ሠራተኞች በሃገራዊ ጉዳይ ውይይት አካሄዱ

ህዳር 09/2017 ዓ.ም



የቱሪዝም ማልጠኛ ኢንስቲትዩት ሠራተኞች "የህልም ጉልበት ለዕምርታዊ እድገት" በሚል መሪ ቃል የብልፅግና 5ኛ ዓመት የምስረታ በዓልን አስመልክቶ እንደሀገር የተሰሩ ሥራዎች እና የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ውይይት አድርገዋል።

የውይይት መድረኩ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በተለይ ከአምስት ዓመት ወዲህ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ሀገራችን በአፍሪካ አህጉረ ውስጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ያለች ሀገር ናት ብለዋል።

ሀገርን እየመራ ያለው የብልጽግና መንግስት በነበሩ ፈተናዎች ያልተንበረከከ ፈተናን ወደ ዕድል በመቀየር ጥበብና ልምድን እያካበተ የመጣ በመሆኑ ታሪካዊት፣ ቀደምትና ስመ ገናና የሆነችውን ሀገራችን ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ለማሻገር እየሰራ ይገኛል ብለዋል። ይህን ለማሳካት ሁሉም የበኩሉን ርብርብና ድጋፍ በማጠናከር እጅ ለእጅ ተያይዞ መስራት እንደሚገባ ገልጸዋል።




የህልም ጉልበት ለዕምርታዊ እድገት በሚል ርዕስ የመወያያ ሰነድ ያቀረቡት የኢንስቲትዩቱ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ እንደ ሀገር የህዝቦች ትብብር፣ የዜጎች ክብር፣ ሀገራዊ ልዕልና እና ሰብዓዊ ብልጽግና ያለባት ሀገር እንዲኖረን የጋራ ህልም ሊኖረን ይገባል ብለዋል።

ሰነዱን መነሻ በማድረግ ከሰላም ጉዳይ፣ የኢኮኖሚ እድገት ከተሳታፊዎች እንደተቋም ወደፊት ሊሰሩ በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ሃሳብና አስተያየት ተሰጥቷል።





## እኛ ያለንን ዕውቀት ለተቋም ካበረከትን ሌሎችም ይህን እንዲያደርጉ እድል እንፈጥራለን ፡፡

አቶ ዳዊት ኃይለሚካኤል





ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የፈተና ሶፍትዌር ሰርተው ባያስረከቡ አቶ ዳዊት ኃይለሚካኤል በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ውስጥ በኢንፎርሜሽን ቴክኖልጂ በመምህርነትና በሪጅስትራር ክፍል ኃላፊነት አጠቃላይ በዘርፉ ወደ አስር ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ተቋሙ አለኝ ከሚላቸው ባለሙያዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡

አቶ ዳዊት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ሰሞኑን የመዘገባቸውን አዳዲስ ሰልጣኞች ለመቀበል ባወጣው ማስታወቂያ 450 የሚሆኑ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ስልጠና ፈላጊዎች የስልጠና መግቢያ ፈተና የተፈተኑበትን የኦንላይን ፈተና ሲስተም አበልጽገዋል፡፡

ሲስተሙን ለመስራት ከሁለት ወር በላይ እንደወሰደባቸው የሚገልጹት አቶ ዳዊት ኃይለሚካኤል ባላቸው አቅም ለተቋሙ አስተዋጽኦ ለማርከት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይህን ሲስተም ሲሰሩ በራሳቸው ተነሳሽነትና የተለየ ክፍያ ሳይጠይቁበት ሰርተው ለሙከራ እንዳቀረቡ ይናገራሉ፡፡

ይህ ስራ ተቋሙ ውስጥ ከፍተኛ አቅም እንዳለ እንዲታወቅና የተቋሙን ገጽታ ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለውም ብለዋል፡፡

የለማው ሶፍትዌር በሀገር አቀፍ ደረጃ የኦንላይን ስልጠና እየተሰጠበት እንዳለው አይነት ስርዓት ያለው ቢሆንም ለማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱና መሰል ተቋማት በሚሆን መልኩ አዲስ የሰሩት የኦንላይን የፈተና ሲስተም ነው፡፡

ሲስተሙ የፈተና ስርቆትን ለማስቀረት የሚያስችል እንዲሁም ለአጠቃቀም ቀላል (user friendly) እንደሆነ አቶ ዳዊት ገልጸዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ የሥልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት በበኩላቸው ሶፍትዌሩ የወረቀት ሥራን የሚያስቀር፣ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ዳዊት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኮምፒውተር ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኢንፎርሜሽን ሳይንስ ሰርተዋል፡፡

## ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች መሰረታዊ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ



ጥቅምት 25/17 ዓ.ም.

በስልጠናው ስለ ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እና ስለ ሳይበር ጥቃትና ደህንነት እንዲሁም መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎችየኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ባለሙያ አቶ ሳሙኤል ገረመው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጥተዋል፡፡

አቶ ሳሙኤል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ዓለም እንዴት እየሰራ እንደሆነ በምሳሌ በማጣቀስ ለሰራተኛው ግንዛቤ የሚሰጡ መልዕክቶችን ሰጥተዋል፡፡

አቶ ሳሙኤል ስለሳይበር ጥቃትና ደህንነት በቂ መረጃ መያዝ ወይም ማወቅ ወቅቱ የሚጠይቀው ዋና ጉዳይ በመሆኑ ተቋሙ በዚህ መልክ መረጃ ለሠራተኞቹ እንዲሰጥ ማመቻቸቱ የሚያስመሰግን ነው ብለዋል፡፡

ስልጠናው ሰፋ ብሎ በቀጣይነት እንዲኖረው ሰራተኛው ጠይቋል፡፡

በስልጠው የሸጋ ትውልድ ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ተገኝተው መረጃውን ሰጥተዋል፡፡



## በየውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ

ታህሳስ 04/2017 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከተለያዩ ክልሎች ለተወጣጡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ሥልጠና ለሚሰጡ አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ። በሥልጠናው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለጹት ይህ አቅም ግንባታ ስልጠና መንግስት ለውጭ ሀገር ስራ ስምሪት የሰጠውን ትኩረት ለማሳካት እና ዜጎች ያለስልጠና ወደ ውጪ በመሄድ የሚደርስባቸውን ያልተመጣጠነ ክፍያ ለማስተካከል እንደሆነና በሀገር ደረጃም ተመሳሳይ ደረጃ ኖሮ ስልጠና የሚሰጡ አካላትን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ ገልጸዋል።

የተቋሙ ስልጠና እና አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት በበኩላቸው ከዚህ በፊት በሁለት ዙር በተለያዩ ክልሎች ያሉ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለሚያሰለጥኑት አሰልጣኞች በተሰጠው ስልጠና የመጣው ግብረመልስ ጥሩ እንደሆነና ዜጎች በአቅራቢያቸው ስልጠና በማግኘት ከሥራ አጥነት በመላቀቅ መንግስት ባመቻቸው እድል እየተጠቀሙ ነው ብለዋል።

ዘንድሮ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለሚሰጡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት ከታቀደው 85 በመቶ መከናወኑም ተጠቅሷል።

ስልጠናው ከEASTRIP ፕሮጀክት ጋር በመተባበር ከክልል ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የተውጣጡ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አሰልጣኞች የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ነው። ስልጠናውን የተቋማችን አንጋፋ አሰልጣኞች በቤት አያያዝና መስተንግዶ ወ/ሮ ህይወት ጥበቡ ፣ በምግብ ዝግጅት ወ/ሮ አወጣሽ ተክሌ እና በምግብና መጠጥ መስተንግዶ አቶ አዶናይ አጥናፉ የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና ተሰጥቷል ።

በEASTRIP ፕሮጀክት ድጋፍ ከተለያዩ ክልል ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ለተወጣጡ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለሚሰጡ ለሦስት ዙር የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።

የኢንስቲትዩቱ የሥልጠና እና የተቋማት አቅም ግንባታ ዴስክ ሀላፊ አቶ ተመስገን በቀለ እንደገለጹት ስልጠናውን ያገኙ አሰልጣኞች ወደ ተቋማቸው ስመለሱ እንደሀገር የተጣለውን ሀላፊነት እንዲወጡ አሳስበው የስልጠናውን ውጤታማነት አፈጻጸም ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ስለ ስልጠናው አስተያየት የሰጡ ተሳታፊዎች ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ወደ ውጭ ሀገር በመሄድ ስራ መቀጠር የሚፈልጉ ዜጎችን በሚገባ ለማሰልጠን እንዲያስችል የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና እድል በማመቻቸቱ እና ለአሰልጣኞችም ያላቸውን ምስጋና አቅርበዋል፡፡

አስተያየት የሰጡት የስልጠናው ተሳታፊዎች እንደሀገር ወጥ የሆነ ስልጠና ለመስጠት በሁሉም ማሰልጠኛ ማዕከላት ያለው የግብዓት አቅርቦት ስጋት እንደፈጠረባቸው ገልጸው ችግሮችን ለመፍታት እንዲያስችል ለተቋማቱ አመራሮች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ስልጠናው በምግብና መጠጥ መስተንግዶ፣ በቤት አያያዝ እና በምግብ ዝግጅት ላይ ያተኮረ ተግባር ተኮር ስልጠና ነው፡፡






ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሀገሪቱ ካሉት የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለሚያሰለጥኑ አሰልጣኞች ስልጠና ሰጠ።

ስልጠናውን አስመልክቶ የእንኳን ደህና መጣች መልዕክት ያስተላለፉት በተቋማችን የEASTRIP አስተባባሪ አቶ አብርሃም ለገሠ እንደገለጹት ይህ ፕሮጀክት በሀገሪቱ በሆቴል ዘርፍ ያለውን የክህሎት ክፍተት በመሙላትና አንዱ ከሌላው ልምድ እንዲለዋወጥ የሚያስችል መሆኑን በመጠቆም በክልሎች ያሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ስልጠናዎች ተመሳሳይ እንዲሆኑ ማድረግና ብቁ የሰለጠነ የሰው ሀይል በመገንባት ለገበያ ለማቅረብ ማሰልጠኛው ከፕሮጀክቱ ጋር እንደሚሰራ ተናግረዋል።

ስልጠናው በሀገሪቱ ካሉት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት 92ቱ ለውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ስልጠና ከሚሰጡት ለመጀመሪያ ዙር 61 እንዲተሳተፉ መደረጉን የተቋሙ ስልጠናና የተቋማት ግንባታ ዴስክ ኃላፊ አቶ ተመስገን በቀለ ገልጿል ።
በመቀጠልም ስልጠናው ዜጎች በያሉበት አገልግሎት እንዲያገኙና ወጥ የሆነ ደረጃ ኖሮት አሰልጣኞችን እንዲያሰለጥኑ ተፈልጎ ነው ብለዋል።ስልጠናው በምግብ ዝግጅት እና ቤት አያያዝ ዙሪያ ለሦስት ቀን ተሰጥቷል፡፡
ስልጠናው የሚሰጠው በተቋማችን አንጋፋ አሰልጣኞች ነው።

**ለላቀ ክህሎት እንተጋለን!**

**We strive for Excellence**

# ኢንስቲትዩቱና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሚገኘውን የቱሪዝም ሀብት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ



**ጥቅምት 10/2017 ዓ.ም**

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዘርፉ የሆቴልና ቱሪዝም ሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ባለፈ ችግር ፈቺ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን እያካሄደ ነው። ኢንስቲትዩቱ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር የክልሉን እምቅ የቱሪዝም ሀብት ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሚገኝ የኢንስቲትዩቱ የጥናትና ምርምር እና ማማከር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ሥዩም ገልጸዋል።

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ በቅርብ ዓመት እራሳቸውን ችለው ከተደራጁ ክልሎች መካከል አንዱ ሲሆን በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት መካከል የጥያ ትክል ድንጋይ እና ለሀይማኖታዊና ተፈጥሮን ለማድነቅ የሚያስችሉ የቱሪስት መስህቦች መገኛ ነው።

ኢንስቲትዩቱ እየሰራቸው ከሚገኙ ሥራዎች መካከል በክልሉ የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችና ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረ ጥናት መካሄዱን የገለጹት አቶ ይታሰብ ጥናቱን መሰረት በማድረግ የቱሪስት ማፕ የተዘጋጀ ሲሆን አንድ ቱሪስት ወደ ክልሉ ቢሄድ ከየት እስከ የት ምን ጎብኝቶ መመለስ እንደሚችል የሚገልገልጽ የቱር ፓኬጅ ሰነድም ተዘጋጅቷል ብለዋል።

እነዚህ ተዘጋጅተው የተጠናቀቁ ሰነዶችን ክልሉ በሚያዘጋጀው መርሃግብር ላይ ርክክብ ይደረጋል ያሉት አቶ ይታሰብ ከዓለም ባንክ EASTRIP ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የተለያዩ ዞኖች ሀገር በቀል የባህል ምግብ ዝግጅት እውቀቶች ምርምር ተደርጓል ብለዋል።

ከዚያ መካከል የሀዲያ ፣ ስልጤ እና በቅርቡ የተሰራው የየም ባህላዊ ምግቦች ተጠቃሽ እንደሆኑ ገልፀዋል። የጥናት ቡድኑ የሚዘጋጁ የባህል ምግቦች የሚዘጋጁበትን ግብዓቶች ዝርዝር ሳይንሳዊ በመሆነ መለኪያ ዘዴ በመጠቀም ከሚያዘጋጁት እናቶች ጋር በመሆን ተገቢውን መረጃ በመውሰድ የምግብ ጥሬ እቃ ዝርዝርና መጠን (ሪሲፒ) ያዘጋጁሉ፡፡

ኢትዮጵያ ለተለያዩ ቱሪዝም አይነቶች የሚሆኑ በቂ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት ናት። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሰፊ ባህልና የምግብ አሰራር ባለባቸው ሀገራት የምግብ ቱሪዝምን ለማስፋፋት የሚያስችል ዕምቅ ሀብት አለ፤ ይሁንና ይህንን የቱሪዝም ዘርፍ ምን ያክል ጥቅም ላይ ውሏል ተብሎ ሲጠየቅ እምብዛም ያልተጠቀምንበት መሆኑን የሚገልጹ ምሁራን በርካታ ናቸው። በዓለም ላይ የምግብ ቱሪዝም በየዓመቱ ከሰባት እስከ 12 በመቶ እድገት እያሳየ ትልቅ ትኩረት እየተሰጠው ያለ የቱሪዝም ዘርፍ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ እነዚህን የባህል ምግቦች ምርምር ማካሄድና መሰነድ ይገባል ይላሉ፡፡ እውቀት በጽሁፍ ካልተቀመጠ ሊረሳ፣ ሊበረዝ ይችላል ፤ የወጭ ሀገር ምግቦች ብቻ ናፋቂ እንዳንሆን የራሳችንን እውቀት ይዘን እዛ ላይ ተጨማሪ ነገሮችን መስራት ይቻላል ፣ ይህ እውቀቱም ለትውልድ ለማሸጋገር ይረዳል ብለዋል፡፡

የባህል ምግቦች የዕሴት ሰንሰለታቸው ሰፊ ነው ፣ ትውልዱ በራሱ ሀብት አየኮራ ሥራ እድልን በመፍጠር የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡የሀገራችን ባህላዊ ምግቦች ተፈጥሯዊ (ኦርጋኒክ) ግብዓቶችን በመጠቀም የሚዘጋጁ በመሆናቸው በጣዕማቸው ቶሎ የሚወደዱ ስለሆነ ለምግብ ቱሪዝም (gastronomy tourism) ትልቅ መሰረት እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

እነዚህ ጥናት የተሰራባቸው የባህል ምግቦች በመጀመሪያ ዙር የተዘጋጁት ለሆቴሎች ተደራሽ እየተደረጉ መሆኑን የገለጹት ም/ዋና ዳይሬክተሩ አሁን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የተሰሩ ምግቦች እንደ መጀመሪያው ዙር ሆቴሎች በምግብ ዝርዝራቸው ውስጥ አስገብቶ አገልግሎት እንዲሰጡበት ይደረጋል ብለዋል፡፡

ይህን ጥናት ማካሄድ እንደ ክልሉም ሆነ አንደ ሀገር እንደ አንድ የሥልጠና መሳሪያ ልንጠቀምበት እንችላለን ያሉት ም/ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ይህን ጥናት ተቀብለው በሆቴሎቻቸው ውስጥ አገልግሎት እየሰጡበት የሚገኙ ሆቴሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የያለው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን የሚሰጥ እንደሆነ ገልጸዋል።

አንድ ጎብኚ ኪሚኖርበት ሥፍራ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ከሚመርጣቸው ነገሮች አንዱ ምግብ እንደ መሆኑ እንደ ሀገርም ብዙ ዓይነት የብሔር ብሔረሰቦች ምግቦች ያሉን በመሆኑ ባህላዊ ምግቦቻችን ላይ እና የምግብ ቱሪዝም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው ይላሉ፡፡

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ባህላዊ ምግቦችና የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች እንዲታወቁ ግንዛቤ በመፍጠር፣ ጥናቶችን በማካሄድ ፣የቱሪዝም ሀብቶች እንዲታወቁ በማድረግና ሌሎችንም ተግባራት በማከናወን የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚገኝ አቶ ይታሰብ ሥዩም ገልጸዋል፡፡

## ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው የኢትዮጵያ ቱሪዝም ሽልማት መርሃ ግብር እውቅና ተሰጠው

ጥቅምት 07/2017 ዓ.ም




በኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር በተዘጋጀው የመጀመሪያ ቱሪዝም ሽልማት መርሐግብር ላይ ኢንስቲትዩቱ ለሀገራችን ቱሪዝም እድገት ላበረከተው አስተዋጽኦ እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከ55 ዓመታት በላይ ለሀገራችን ቱሪዝም ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ሀይል በማቅረብ፣ በዘርፉ ያልተቋረጠ ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወንና የማማከር አገልግሎትን በመስጠት ለዘርፉ እድገት እያበረከተ ለሚገኘው ጉልህ አስተዋጽኦ ሽልማት ተበርክቶለታል።

ኢንስቲትዩቱ በሆቴልና ቱሪዝም ሙያ መስኮች ላይ ያተከሩ ከደረጃ እስከ ዲግሪ ያሉ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ሲሆን ፣ በተለይ የገበያ ፍላጎት ፣ በኢንዱስትሪው ላይ ያለውን በዘርፉ የሰለጠን የሰው ሀይል ብዛት በጥናት እየለየ ለመንግስት ፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ እንምዲሁም የቱሪዝም ዘርፉ ለስራ እድል ፈጠራ ያለውን አስተዋጽኦ በማጥናት የመንግስትና የግሉን ዘርፍ የሚጠቅሙ ጥናቶችን ተደራሽ እያደረገ እንደሚገኝ በእውቅና መርሐ ግብሩ ላይ ተገልጿል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ለኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር መመስረት የነበራቸው አስተዋፅኦም ከፍ ያለ እንደሆነም በሽልማት መርሃ ግብሩ ላይ ተገልጿል፡፡

በመርሃ ግብሩ ላይ ለሀገራችን ቱሪዝም እድግት አስተዋጽኦ ያደረጉ ተቋማትና ግለሰቦች ተሸልሟል፣ በቀጣይነትም በተጠናከረ ሁኔታ የሚቀጥል እንደሆነ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡



**የአጫጭር ትምህርት መርሐ ግብር የተግባር ስልጠና ከሼፍ ቴዎድሮስ መስፍን ጋር**

## ኢንስቲትዩቱ እየሰጠ በሚገኘው አገልግሎት ላይ የተገልጋይ እርካታን ለመጨመር የችግር አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ለአስተዳደር ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ



የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እየሰጠ በሚገኘው የስልጠና፣ የምርምርና ማማከር አገልግሎቶች ላይ የደምበኞችን እርካታ ከፍ ለማድረግ እንዲያስችል ለአስተዳደር ሰራተኞችና ማኔጅመንት አባላት በችግር አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ላዙሪያ በ #EASTRIP ፕሮጀክት አስተባባሪነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ ፡፡

ስልጠናውን ያስጀመሩት የኢንስቲትዩቱ የአመራርና አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ስልጠናው ሁሉም ሰራተኛ በተመደበበት ቦታ የበላይ አመራር ሳይጠብቅ ሀላፊነት እንዲወጣ እና ባለሙያው የሚያጥሙ ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዝ እንደሆነ በመጠቆም ስልጠናው በቂ የልምድ ልውውጦች የሚደረጉበት ነው ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ ይዞራል



**ፕሮጀክቱ ከሰራተኞች አቅም ማጎልበቻ ባሻገር ኢንስቲትዩቱ የልህቀት ማዕከል ለመሆን እየሰራ የሚገኘውን እቅድ ለማሳካት ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ተገለጸ፡**

EASTRIP ፕሮጀክት ከሰራተኞች አቅም ግንባታ ባሻገር ለኢንስቲትዩቱ የተሰጡ ተልዕኮዎችን እንዲሁም ከትላንት ጀምሮ በተሰጠው ስልጠና ወቅት የተለዩ ችግሮችን በመፍታት ተልዕኮውን እንዲወጣ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ አብርሀም ለገሰ ገለጹ።

ከታህሳስ 26 ጀምሮ እየተሰጠ ነበረው የችግር አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ስልጠና መጠናቀቁን ተከትሎ ስልጠናው በተቋም ደረጃ የሚታዩ ወቅታዊ ጉዳዮችን ለመተንተና ችግሮችን ለመለየት የሚያግዝ እንደሆነ የገለጹት አቶ አብርሃም ለገሰ ተመሳሳይ አቅም ግንባታ ስልጠናዎች በቀጣይነት ይሰጣሉ ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ፕሮጀክቱ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ፣ የኢንዱስትሪውን ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የስልጠና ማኑዋሎች እንዲዘጋጁ ማድረጉን ያስታወሱት የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ኢንስቲትዩቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ እንዲሰራ፣ ስልጠናዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ በአጠቃላይ ኢንስቲትዩቱን ወደ ልህቀት ማዕከል ሊያሻግሩ የሚያስችል ድጋፍ እየተደረገ እንደሆነ አብራርተዋል ።

ስልጠናው ላይ ከተሳተፉት መካከል የቮኬሽናል ጋይዳንስና ትብብር ስልጠና አስተባባሪ አቶ ታደሰ ሞላ በበኩላቸው የተሰጠው ስልጠና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ምቹ የስራ ቦታን ለመፍጠር እየሰራና የሪፎርም ስራዎች እየተካሄዱ ባለበት በመሆኑ ወቅታዊ እንደሆነ ገልጸዋል።

በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ውስጥ የታቀዱ ስራዎች ሁሉንም በሚያሳትፍ መልኩ መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰራተኞች በቀላሉ ለማሳተፍ ያግዛል ያሉት አቶ ታደሰ ሞላ የተቋሙ እቅዶችን ለማሳካት በቅንጅት መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በስልጠናው ላይ በግብዓት፣ በቅንጅታዊ አሰራር፣ እቅድን መሰረት አድርጎ ከመስራትና ሌሎችም ኢንስቲትዩቱ ተልዕኮውን በአግባቡ እኔዳይወጣ በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ሰራተኞችም በቀጣይነት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።

## ጥቂት ካነበብነው ስለ ኢትዮጵያ

ወደ ገነት መዳረሻ መንገዱ በኢትዮጵያ በኩል ነው ፤ወደ ገሀነም መግቢያ በሩም በኢትዮጵያ ግርጌ ስር ነው ተብሎ ይታመናል።

- **ዓባይ ወንዝ** ከደጋ ተነስቶ ወይና ደጋ ቆላና በረና አያቆራረጠ ረዥም መንገድ የሚጓዝ የአለማች ረጅሙ ወንዝ ነው።

* **ኤርታ ኤሌ** - አሳታዊ ሀይቅ ህይወት የሚባል የማይገኝበት እሳቱን የማይጠፋ የአለማችን እጅግ ሞቃታማ ስፍራ ነው። ኤርታ ኤሌ ማለት በአፋርኛ የሚጨስ ተራራ ወይም የገሀነብ መግቢያ ማለት ነው።













## ኢንስቲትዩት ከአማካሪ ቦረዱ ጋር ውይይት አካሄደ

ጥቅምት 2/2017 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2017 ዓ.ም የሶስት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም እና ኢንስቲትዩቱ ያጠናውን በቱሪዝምና ሆቴል ዘርፍ ያለውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ስምሪት እና የገበያ ፍላጎት ለኢስትሪፕ(EASTRIP) ፕሮጀክት ቴክኒካል አማካሪ ቦርድ አቅርቦ ምክክር አካሄደ።

የምክክር መድረኩን የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ሲከፍቱ እንደተናገሩት አማካሪ ቦርዱ ከተቋቋመ ጀምሮ በቱሪዝምና ሆቴል ዘርፍ በትብብር ስልጠና፣ በአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሁም በሁሉም ሙያዊ ድጋፍ በሚያስፈልጉን ሁሉ ድጋፋችሁ አልተለየንም ብለዋል።
አቶ ጌታቸው አክለውም ኢንስቲትዩቱ ያሉትን የዘርፉን አሰልጣኞችና አማካሪ ቦረዱን በመጠቀም በዘርፉ የሚታየውን የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በአጫጭር ስልጠና ሥራ ያላገኙ የዩንቨርሲቲ ምሩቃንን ለማሰልጠን፣ ከአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር የቱሪስት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን ስልጠና ለመስጠት እና ከህፃናት አያያዝ ጋር የሚስተዋለውን የሰው ሃይል እጥረት ለመቅረፍ የሚያስችል የሞግዚት ስልጠና በዚህ በጀት ዓመት ሊሠሩ የታቀዱ እንደሆኑ ገልጸዋል።
የቴክኒካል አማካሪ ቦርዱ ሰብሳቢ አቶ መልካሙ መኮንን እንደተናገሩት ኢንስቲትዩቱ እኛን በሚፈልግበት የትኛውም ጉዳይ ላይ ተገኝተን ሙያዊ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን ካሉ በኋላ በተለይ ተቋሙ ከመደበኛው ስልጠና ባሻገር በአጫጭር ሊሠራ ያቀዳቸውን ስልጠናዎች ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የሀገርን ገጽታ ለመገንባት ያለው አስተዋጾ የጎላ ነው ብለዋል። የኢስትሪፕ(EASTRIP) የሶስት ወር አፈፃፀም ሪፖርት ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ አብርሃም ለገሰ ፤የጥናት ጽሑፉን ደግሞ የኢንስቲትዩቱ የጥናትና ምርምር ዘርፍ አቶ ይታሰብ ስዩም አቅርበዋል። የአማካሪ ቦርዱ ከመንግስትና ከግሉ ዘርፍ እንዲሁም ከቱሪዝምና ሆቴል ማህበራት የተቀናጀ ll አባላት ያሉት ነው።

# ኢንስቲትዩቱ ከዌልነስ ሜዲካል ኮሌጅ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ







ኢንስቲትዩቱ ከዌልነስ ሜዲካል ኮሌጅ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

ቱ.ማ.ኢ. ህዳር 3/2017ዓ.ም

የፌዴራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከዌልነስ ሜዲካል ኮሌጅ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ።

በመግባቢያ ስምምነቱ ላይ በመገኘት የፈረሙት የኢንስቲቲዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ እንደገለፁት የኢንስቲትዩቱ ፍላጎትን መሠረት ያደረጉ የረጅምና የአጭር ጊዜ ስልጠና ከመላው ሀገሪቱ መጥተው የሚሰለጥኑበት መሆኑን በመጥቀስ ይህ ስምምነት ወቅቱ የሚፈልገውን የስፓና የማሳጅ አገልግሎት የሚሰጡ ስልጡን ባለሙያዎችን ለማፍራት ዓላማ እንዳለው ገልፀዋል።

የዌልነስ ሜዲካል ኮሌጅ ባለቤት ዶ/ር ሰላም አክሊሉ በበኩላቸው ስልጠናው በሀገር ደረጃ በቱሪዝም ዘርፍ እንዲሰጥና በየሆቴሎቹም የሚገኙ ባለሙያዎች ይህን ስልጠና ሳይወስዱ እንዳይሰሩ መደረግ እንዳለበት፣ ለዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ጥረት ማድረጋቸውን አንስተዋል። በሆቴልችና በአንዳንድ ቦታዎች እየተሰጡ ያሉ የማሳጅ አገልግሎቶች የሀገርን ስም ከማጉደፋቸው ባሻገር የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ያለው ተፅእኖ ቀላል አይደለም ብለዋል።

ከዌልነስ ሜዲካል ኮሌጅ ጋር የተፈረመው የመግባቢያ ስምምነት በስልጠና ዘርፍ አብሮ ለመስራት የሚያስችል ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜም በአጫጭር ስልጠና ዘርፍ የስድስት ወር ስልጠና የሚጀምሩ ይሆናል።

በቀጣይ የሰልጣኞችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ወደ ደረጃ የማሳደግ ፍላጎት መኖሩን የስልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት ተናግረዋል።

## ለሆቴሎችና አስጎብኚ ድርጅቶች የማማከር አገልግሎት ተሰጠ ።





ጥቅምት 1/2017 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በአራት ከተሞች ማለትም በመቀሌ ፣በአክሱም፣ በአዳማ እና ቢሾፍቱ ከተሞች በሚገኙ ሆቴሎችና ሪዞርቶች እንዲሁም አስጎብኚ ድርጅቶች የማማከር አገልግሎት እየተሰጠ ነው፡፡

የተቋሙ የማማከር እና ማርኬቲንግ ዴስክ ኃላፊ አቶ ታምራት ተፈራ እንደገለፁት ተቋሙ ከተሰጠው ተለዕኮ አንዱ የማማከር ሙያዊ ድጋፍ በመሆኑ ከአሰልጣኞች እና ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት በተለያዩ ከተሞች በሚገኙ ሆቴሎች እና አስጎብኚ ድርጅቶች የማማከር አገልግሎት እየተሰጠ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በዛሬው እለት በተለያዩ ከተሞችና ሆቴሎች የማማከር አገልግሎት የተሰጠባቸው በመስተንግዶ ፣እንግዳ አቀባባልእና የምግብ ዝግጅቶች ዙሪያ የሚታዩ ክፍተቶችን እንዲያሟሉ እና መልካም ተሞክሮዎች እንዲቀጥሉ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

በአዳማ ከተማ ራስ አዳማ ሆቴል ኦፕሬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌትነት እና አዳማ ጀርመን ሆቴል ሥራአስኪያጅ አቶ ለገሰ ንጉሱ በተመሳሳይ ለሆቴሎቻቸው በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ማጣት እና የሰለጠኑት ባለሙያዎችም አንድ ቦታ ረግቶ አለመሥራት ችግሮች እንዳሉ ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ በየጊዜው የሚያደርጓቸው የተግባር ላይ ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት መቀጠል እንዳለበት ሲሉ አሳስበዋል፡፡ ይህ የማማከር አገልግሎት በሁሉም ከተሞች ባሉ ሆቴሎችና አስጎብኚ ድርጅቶች እንደሚቀጥልም ተገልጿል ።

## የማጠናከር ዘመን (consolidation Year)





ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተገለጸ፡፡

ቱ.ማ.ኢ

ጥቅምት 26/2017 ዓ.ም

የኢንስቲቲዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ ይህ የያዝነው ዓመት የማጠንከር ዘመን/ዓመት ተብሎ መሰየሙን ገለጹ፡፡ በትምህርትና ስልጠና ፣በስልጠና ጥራት ፣የአጫጭር ስልጠና የቅበላ አቅምን ማሳደግ፣ የበጀት እጥረትን ሊቀርፉ የሚችሉ በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ላይ ገቢ የሚያመነጩ፣ ህብረተሰብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎችን በማጠናከር ፤በዘርፉ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ፤ በዘርፉ የማማከር አገልግሎት በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚና ተወዳዳሪ ሆኖ መሥራት ላይ አጠናክረን የምንይዛቸው አበይት ጉዳዮቻችን መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ለተግባራዊነቱም በቴክኖሎጂ እና በ System thinking ሁሉን አቀፍ የሆኑ ወደፊት የሚያራመዱ የሃሳብ ማመንጫ ማዕከሎችን በማጠናከር ሁሉም ሰራተኛ እና ባለድርሻ አካል ተሳትፎ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ የባለፈውን በጀት ዓመት ዓመተ ምርታማነት በሚል መሪ ቃል ምርታችን ሰልጣኞቻችን ናቸው ብለን በልዩ ትኩረትመሥራታችን ይታወቃል፡፡

## በአራት ከተሞች ይሰጥ የነበረው የማማከር አገልግሎት መጠናቀቁን ተከትሎ ውጤቱ ተገመገመ።




ቱ.ማ.ኢ. ጥቅምት 12/2017 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በትግራይ ክልል በመቀሌ እና አክሱም ከተሞች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ደግሞ በአዳማና ቢሾፍቱ ከተሞች ለሚገኙ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ሆቴሎች ፣ሪስቶራንቶችና የቱሪዝም አስጎብኚ ድርጅቶች ይሰጥ የነበረው የማማከር አገልግሎት ተጠናቀቀ።

ኢንስቲትዩት ከየክልሎቹ ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በመተባበር በአራት ቡድኖች የተቋሙን አሰልጣኞች ከሆቴልና ቱሪዝም ማህበራት ተወካይ ባለሙያዎች ጋር በማቀናጀት የተሰጠውን የማማከር አገልግሎት ከአማካሪ ቡድኑ ጋር በዛሬው ዕለት ገምግሟል፡፡

የማማከርስራው በዋናነትም፣ በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ወጭ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ አሰራር እንዲከተሉ የሚያግዝ የአቅም ግንባታ ሥራ መሆኑን የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይታሰብ ሥዩም ገልጸዋል፡

ከዚህም በተጨማሪ በተቋሙ እና ከልዩ ልዩ ማህበራት በመጡ ባለሙያዎች መካካል የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስቻለ ጭምር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአራቱም ከተሞች በአጠቃላይ 58 ሆቴሎችና ሪዞርቶች፣ 14 ምግብ ቤቶች እና ስድስት የቱሪስት ድርጅቶችና ማህበራት በድምሩ 78 ተቋማት አገልግሎቱ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ሁሉም የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት በተሰጣቸው አገልግሎት ደስተኞች እንደነበሩ የአማካሪ ቡድኑ አባላት ተናግረዋል፡፡

በዚህ የማማከር ሥራ አብዛኛው ተቋማት የሰለጠነ የሰው ሀይል ጉድለት እንዳለባቸው ገልጸው የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ሙያዊ ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠይቋል፡፡ በቀጣይም በሌሎች ክልሎች፣ ከተማዎች እና የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ለሚገኙ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መሰል ድጋፍ እንደሚደረግ አቶ ይታሰብ ተናግረዋል ።

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2017 ዓ.ም አዲስ ተማሪዎች አቀባበል ተደረገ






.ህዳር 13/2017 ዓ.ም

ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2017 ዓ.ም አዳዲስ ሰልጣኞች አቀባበል አደረገ። በአቀባበሉ ፕሮግራም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያቀረቡት የተቋሙ የስልጠና እና አቅም ግንባታ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት እንደተናገሩት ወደዚህ አንጋፋ ተቋም በመቀላቀላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ካሉ በኋላ ተቋሙ ከሌሎች ተቋማት ለየት የሚያደርገው በተግባር የተደገፈ እና በተለያዩ ሶፍትዌር የታገዙ ቤተሙከራዎች ስልጠና መስጠቱ መሆኑን ገልጸው እንዲሁም በዘርፉ ብቃት ያላቸው አሰልጣኞች መኖራቸው እንደሆነ ገልፀው ፤ከሰልጣኞች የሚፈልገው ለኢንደስትሪው የሚመጥን ስነምግባር መላበስ እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

የተቋሙ ሾኬሽናልና ጋይዳንስ እና የትብብር ስልጠና አስተባባሪ አቶ ታደሰ ሞላ ስለትብብር ስልጠና ግንዛቤ ሰጥተዋል።

የሬጅስትራርና አልሙኒም ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ታምራት ወልዴ፣ የሆቴል ፋካልቲ ዲን አቶ ዮናስ ቶሎሳ ፣ የቱሪዝም ፋካሊት ዲን ተወካይ አቶ ማሩ እማኙ እንዲሁም የተቋሙ ስነምግባር ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ ወ/ሪት ዓለምፀሐይ በቀለ ጨምሮ በስልጠና ወቅት እንደ ዲፓርትመንት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሰፊ ግንዛቤ በመስጠት ሰልጣኞችም ያልተረዱትን በመጠየቅ ወይይት ተደርጎበታል።

# ኢንስቲትዩቱ አዲስ የሰልጣኞች መማክርት አቋቋመ









ታህሳስ 04/2017 ዓ.ም የኢንስቲትዩቱ ስልጠናና አቅም ግንባታ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት ኢንስቲትዩቱ በክህሎት ፣ ሥነምግባር እና ዕውቀት ሰልጣኞቹን የሚያንጽ በመሆኑ ይህን በሚገባ ለመወጣት፤ የስልጠና ጥራትን ለማስጠበቅ የሰልጣኞች መማክርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል።

ስልጠናውን ስትከታተሉም ሆነ በትብብር ስልጠና በምትሰማሩበት ቦታ ተቋማችሁን ከፍ የሚያደርግ ተግባር ላይ እንድትገኙ የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

በኢንስቲትዩቱ የስልጠና ጥራትን ለማስጠበቅ የሰልጣኞች መብትና ግዴታን በሚመለከት ስልጠና የሰጡት የስልጠና ጥራት ማረጋገጫ ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር አስቻለው አደራ ስልጠናው እየተካሄደ ያሉ የጥራት መለኪያ መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የተሻለ የስልጠና ሂደት እንዲኖር እንዲሁም ከስልጠና በኋላም ያሉ ክፈተቶችን መለየት ከሰልጣኞች ይጠበቃል ብለዋል። አሰልጣኞችም ዝግጅት በማድረግ፣ ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ ስልጠና መስጠት ይገባቸዋል ብለዋል።

የቮኬሽናል ጋይዳንስ ፣ ካውንስልንግ አስተባባሪ አቶ ታደሰ ሞላ በበኩላቸው የሰልጣኞች ካውንስል መቋቋሙ በተለይ በትብብር ስልጠና ላይ ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እና ሰልጣኞች ጋር ተደራሽ ለመሆን ያግዛል ብለዋል።

በሰልጣኞች ሥነምግባር መመሪያ፣ የሴቶች እኩልነትና ትንኮሳ መከላከል እና የስልጠና ጥራትን በሚመለከት አጠቃላይ መረጃ ተሰጥቷል። በመጨረሻም አስር ቋሚ እና ሶስት ተጠባባቂ አባላት ያሉት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰልጣኞች መማክርት ተመርጠው የሥራ አቅጣጫ ተሰጥቷቸዋል።

# የኢንስቲትዩቱ ሰልጣኞች የብሔር ብሔረሰቦችን በዓል አከበሩ







ታህሳስ 1/2017 ዓ.ም

የፌዴራል ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰልጣኞች 19ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች አከበሩ። የኢንስቲትዩቱ የሥራ አመራር እና አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ለሰልጣኞች ባስተላለፉት መልዕክት ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት" ትንሿ ኢትዮጵያ" ናት ከየትኛውም የሀገሪቱ ክልሎች የመጡ ሰልጣኞች የሚስተናገዱበት፣ በስልጠና እና በሥራው ዓለም ሲሰማሩ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ባህል፣ቅርስ የሚያስተዋውቁ እንዲሁም ከተለያየ የዓለም ክፍልም ሆነ የሀገራችን ጎብኚ እንግዳ የሚቀበሉና የሚያስተናግዱ ባለሙያዎችን የሚያፈራ በመሆኑ ኢትዮጵያን ለማወቅና ለማስተዋወቅ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋልብለዋል።

ም/ዋና ዳይሬክተሩ አክለውም ቱሪዝም ለሰላም ሰላም ለቱሪዝም የጀርባ አጥንት ነው። በሀገራችን ቱሪዝም ከአምስቱ የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ሆኖ በልዩ ትኩረት እየተሰራ ያለው ሥራ የሚደነቅ ነው፤ በዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ሁላችንም ለሰላም ዘብ መቆም አለብን ብለዋል።

ሰልጣኞች በተለያየ የብሔር ብሄረሰቦች ባህላዊ አልባሳት እና ጨዋታ ደምቀው በዓሉን ያደመቁት ሲሆን በዓሉ በሻማ ማብራት እና በኢትዮጵያ ባንዲራ ያሸበረቀ ኬክ እና ዳቦ በመቁረስ ስበዓሉ ተፈጽሟል።